# በጋራ ኢንቨስትመንት "Joint Investment" በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ዉክልና ስራ ከዉጭ አገር ኩባንያዎች ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች

## 1. መግቢያ

የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 549/99 መሠረት ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነት ውስጥ አንዱ በዕቃ ማስተላለፍ እና የመርከብ ውክልና ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችን መቆጣጠርና ብቃታቸውን ማረጋገጥ አንዱ ነው።

ይህንንም ኃላፊነቱን ለመወጣት ደንብ ቁጥር 37/90 መሠረት ያደረገ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት በማውጣት በዕቃ ማስተላለፍ፣ በመርከብ ውክልና ወይም በሁለቱም የሥራ መስኮች ለሚሰማሩ ድርጅቶች ብቃት የማረጋገጥ፣ የማደስ እና የመሠረዝ ተግባራትን ያከናውናል።

የዕቃ ማስተላለፍ፣ የመርከብ ውክልና ወይም ሁለቱም የሥራ መስኮች ቀደም ሲል በደንብ ቁጥር 37/90 እንዲሁም በኢንቨስትመንት ደንብቁጥር 270 ላይ እንደተገለፀው ለኢትዮጵያውያን (የኢትዮጵያ ዜግነት ላላቸው) እና በተመሳሳይ ሥራን ለኢትዮጵያውያን ክፍት ለአደረጉ ሌሎች አገራት ዜጎች ብቻ የተወሰነ ሥራ በመሆኑ ላለፉት 21 ዓመታት በዚህ አግባብ ሲሰራ ቆይቷል።

ሆኖም ግን የአገራችን የሎጅስቲክስ አፈፃፀም በዓለም ደረጃ በዝቅተኛ ደረጃ ከመመደቡ አንፃር የአገራችንን የውጪ ንግድ በአግባቡ ሊደገፍ ባለመቻሉ ምክንያት መንግሥት ይኼን ለአገር ውስጥ ባለሀብት ብቻ ተከልሎ የነበረው የሥራ ዘርፍ ኢትዮጵያውያን ከሌላው የውጭ አገር ዜጎች ጋር በጋራ እንዲሰሩ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቷል።

የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 ለማሻሻል በወጣው 849/2006 አዋጅ አንቀጽ 4 ላይ ለኢንቨስትመንት ቦርድ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ከላይ



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Maritime Affairs Authority

የጠቀስናቸውን የሥራ መስኮች የኢንቨስትመንት ኮሚሽን በቁጥር 2/2010 ባወጣው መመሪያ መሠረት ኢትዮጵያውያን ከውጭ አገር ዜጎች ጋር 51% ለ49% የሆነ ድርሻ እንደ ቅድመተከተላቸው በመያዝ በጋራ በኢንቨስትመንት ደረጃ እንዲሰማሩ ፈቅዷል፡፡

ይህንን የመንግሥት ውሳኔ ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር የኢንቨስትመንት አዋጅ መሠረት በማድረግ ወደ ሥራው ለሚገቡ ኢትዮጵያውያን እና የውጭ አገር ዜጎች የሚመሠረተውን ድርጅት ብቃት ለማረጋገጥ እንዲሁም የተወሰደው ማሻሻያን ሊሳካ ያሰበው ዓላማ ታሳቢ ያደረገ የብቃት መረጋገጫ መስፈርት ማዘጋጀት በማስፈለጉ ባለሥልጣኑ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መስፈርት አዘጋጅቷል፡፡

## 2. ትርጉም

2.1. **የጋራ ኢንቨስትመንት "Joint Investment"**፡-ማለት በአዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 12 (1)(ለ) ላይ እንደተመለከተው በቅንጅት ኢንቨስት የሚያደርጉ የአገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ባለሀብቶች ማለት ነው፡፡

2.2. **ተዛማጅ የትምህርት መስኮች**፡-ማለት በተዘዋዋሪ ከዘርፉ ጋር ግንኙነት ያለው ትምህርት ሲሆን እንደ አግባብነቱ እየታዬ በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚወሰን ነው፡፡

## 3. በሁለቱም የስራ መስኮች ለመሰማራት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

3.1. ባለስልጣን መ/ቤቱ የሚያዘጋጀውን የቃል መግቢያ ሰነድ እና የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት እና በመፈረም ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

3.2. ከዉጭ ሀገር በጋራ ኢንቨስትመንት "Joint Investment" ለመስራት የገባዉ ኩባንያ በሀገር ዉስጥ ኢንቨስት እንዲያደርግ በኢንቨስትመንት ኮሚሽን የተሰጠዉን ፈቃድ ኮፒ ማቅረብ ይኖርበታል፣

3.3. የዉጭ ኩባንያዉ የተመዘገበበት ሀገር እና የስራ ፈቃድ ኮፒ ማቅረብ፣

3.4. የዉጭ ኩባንያዉ እና የሀገር ዉስጥ ኩባንያዉ የጋራ ኢንቨስትመንት "Joint Investment" ዉል ስምምነት (መመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ) በሰነዶች ምዝገባ ኤጀንሲ የጸደቀ ኮፒ፣

3.5. የዉጭ ኩባንያዉ በዘርፉ ቢያንስ ለ 10 ዓመታት የሰራ እና ይህንኑ የሚገልጽ ማስረጃ ኮፒ ከኩባንያዉ ዋና መስሪያቤት ሀገር ፈቃድ ሰጭ አካል ማቅረብ የሚችል፣የሀገር ውስጥ ኩባንያው ደግሞ ቢያንስ በዘርፉ 5 ዓመት የሰራ ሆኖ ይህም ከባለስልጣን መ/ቤቱ ዳታ ቤዝ የሚረጋገጥ ይሆናል፡፡

3.6. የጋራ ኢንቨስትመንት "Joint Investment" ኩባንያዉ ከ5000 ካሬ ሜትር ያላነሰ ቦታ ላይ ያረፈ የእቃ ( ኮንቴይነር) ማስተናገጃ እና ማከማቻ የሚሆን የኮንቴይነር ተርሚናል እና የጥቅል እቃ ማቆያ መጋዘን አድራሻ እና ይዞታ የሚገልጽ ካርታ ወይም በሰነዶች ምዝገባ ኤጀንሲ የተመዘገበ የኪራይ ዉል ማቅረብ፣

3.7. በዉጭ ኩባንያዉ በኩል ከዉጭ ሀገር የሚቀጠሩ ባለሙያዎች ቢያንስ የ10 ዓመት ልምድ ያላቸዉ ሆኖ በሺፒንግ ማኔጅመንት፣ፖርት ማኔጅመንት፣ሎጂስቲክስ እና ሰፕላይ ቸን ማኔጅመንት፣ በትራንስፖርት፣ በቢዝነስ አስተዳደር፣ በማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም፣ በማሪታይም ህግ፣ በማሪታይም አስተዳደር እና ተዛማጅ መስኮች ከታወቀ የትምህርት ተቋም ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ እና ከዚያ በላይ መያዝ የሚኖርባቸዉ ሲሆን የሰራተኞች CV እና የትምህርት ማስረጃ ኮፒ ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፣

3.8. የዉጭ ኩባንያዉ ወደ አገር ዉስጥ ሲገባ የሀገሪቱን ሎጂስቲክስ ለማዘመን የሚጠቀምባቸዉን የIT ዉጤቶች እና የእቃ ማንቀሳቀሻ ማሽነሪዎች ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀዉ ቅጽ መሰረት ማስመዝገብ ይኖርበታል፣



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Maritime Affairs Authority

3.9. የጋራ ኢንቨስትመንት "Joint Investment" ድርጅቱ ለሀገሪቱ እና ለዜጎች ቢያንስ በቀጣይ 5 ዓመታት የሚያስገኘዉን ጥቅም ያካተተ የቢዝነስ ፕላን አዘጋጅቶ 1 ኮፒ ማቅረብ ይኖርበታል፣

3.10. በመርከብ ዉክልና ስራ እና በእቃ አስተላላፊነት ስራ (በሁለቱም) ላይ ከዉጭ ሀገር ኩባንያ ጋር በጋራ ኢንቨስትመንት "Joint Investment" ለመስማራት የሚፈልግ የዉጭ ሀገር ኩባንያ 250,000 የአሜሪካን ዶላር በቀጥታ በሀገር ዉስጥ ባንኮች ያስገባበትን የባንክ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፣

3.11. በሁለቱም የስራ መስኮች ማለትም መርከብ ዉክልና ስራ እና በእቃ አስተላላፊነት ስራ ላይ ከዉጭ ሀገር ኩባንያ ጋር በጋራ ኢንቨስትመንት "Joint Investment" ለመስራት ፍላጎት ያለዉ የሀገር ዉስጥ ኩባንያ 260,204 የአሜሪካን ዶላር በወቅቱ የኢትዮጵያ ብር ምንዛሬ መሰረት ካፒታል ያለዉ ሆኖ ከዚህ ዉስጥ 150 ሺህ የአሜሪካ ዶላር በጥሬ ገንዘብ መኖሩን ከባንክ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል። ቀሪዉ 110,204 የአሜሪካን ዶላር ግምት በአይነት መቅረብ የሚችል ሆኖ ንብረቱ በባለስልጣኑ ባለሙያዎች የሚረጋገጥ ይሆናል፣

3.12. የጋራ ኩባንያው በዉጭ ሀገራት ስራዉን ለማቀላጠፍ የሚጠቀምባቸዉን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መክፈት ይኖርበታል፣ ለዚህም ቢያንስ የ5 የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን የስራ ፈቃድ ኮፒ በማቅረብ፤ ስምና ዝርዝር አድራሻ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በሚያዘጋጀዉ ቅጽ መሰረት ማሳወቅ ይኖርበታል፣

3.13. የሀገር ውስጥ ኩባንያው በድንበር ተሻጋሪነት ስራ እንዲሰሩ በትራንስፖርት ባለስልጣን ፈቃድ የተሰጣቸዉ ከ50 ያላነሱ ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት ፈቃድ (ሊብሬ) የሚያቀርብ ፤ ከ3 ያላነሱ ፒክአፕ (አዉቶሞቢል) መኪኖች ሊብሬ ማቅረብ የሚችል፣ ወይም የተጠቀሱት ንብረቶች ካለው ከሌላ ድርጅት ጋር የኮንትራት ውል በመያዝ የውሉን ኮፒ ማቅረብ የሚችል፤ወይም በ6(ስድስት) ወራት

ጊዜ ዉስጥ ማቅረብ የሚችል መሆኑን ማረጋገጫ የሚሰጥ፣ በሀገር ዉስጥ ስራ የሚያከናዉንበት ዘመናዊ የመረጃ ማስተላለፊያ ቴክኖሎጂዎች የተሟላ ቢሮ ያለዉ (ኮምፒዩተር፣ፋክስ፣ገመድ አልባና ባለገመድ ኢንተርኔት፣ኮፒየር)

3.14. በገንዘብ ሚኒስቴር ጸድቆ ስራ ላይ የዋለውን የአገልግሎት ዋጋ ለባለስልጣን መ/ቤቱ መክፈል እና ደረሰኝ ማቅረብ ይኖርበታል።

## 4. በመርከብ ውክልና የአገልግሎት መስክ ብቻ በጋራ ኢንቨስትመንት "Joint Investment" ለመሰማራት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ - ሁኔታዎች

4.1. ከላይ በተራ ቁጥር 10፣11 እና 13 ከተጠቀሱት በስተቀር ከ1-12 ያሉትን በሙሉ ማሟላት ይኖርበታል።

4.2. የዉጭ ኩባንያዉ ከሀገር ዉስጥ ኩባንያ ጋር የ49 % ድርሻ ዉል ይዞ ሲገባ 150,000 የአሜሪካ ዶላር በቀጥታ በኢትዮጵያ ዉስጥ በሚገኙ ባንኮች ያስገባበትን የባንክ ደረሰኝ ማቅረብ የሚችል መሆን ይኖርበታል፣

4.3. የሀገር ዉስጥ ኩባንያ ከውጭ ሀገር ኩባንያ ጋር በጋራ ኢንቨስትመንት "Joint Investment" ለመስራት 156,123 የአሜሪካን ዶላር ካፒታል ያለው ሆኖ ከዚህ ውስጥ 100 ሺህ ዶላሩ በብር በባንክ መኖሩ ከባንክ ማስራጃ የሚቀርብ ሲሆን 56,123 ዶላሩ በአይነት መቅረብ የሚችል ሆኖ ንብረቱ በባለስልጣኑ ባለሙያዎች የሚረጋገጥ ይሆናል፣

4.4. ኩባንያዉ በደንብ ቁጥር 37/1990 ከተዘረዘረዉ የመርከብ ዉክልና ስራ በተጨማሪም የሚከተሉትን ማከናዎን ይኖርበታል፣

4.4.1. በሀገር ዉስጥ የዕቃ መጫኛ ሰነድ (Bill of Lading) ለደንበኛዉ መስጠት፣

4.4.2. በሀገር ዉስጥ ጭነትን የመረከብ አገልግሎት መሥጠት

## 5. በእቃ አስተላላፊነት የአገልግሎት መስክ ብቻ በጋራ ኢንቨስትመንት "Joint Investment" ለመስማራት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ - ሁኔታዎች

5.1. ከላይ በተራ ቁጥር 10 እና 11 ከተጠቀሱት በስተቀር ከ1-13 ያሉትን በሙሉ ማሟላት ይኖርበታል፡፡

5.2. የዉጭ ኩባንያዉ ከሀገር ዉስጥ ኩባንያ ጋር የ49 % ድርሻ ዉል ይዞ ሲገባ 200,000 የአሜሪካ ዶላር በቀጥታ በኢትዮጵያ ዉስጥ በሚገኙ ባንኮች ያስገባበትን የባንክ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል መሆን ይኖርበታል፣

5.3. የሀገር ዉስጥ ኩባንያ ከውጭ ሀገር ኩባንያ ጋር በጋራ ኢንቨስትመንት "Joint Investment"ለመስራት 208,163 የአሜሪካን ዶላር ካፒታል ያለው ሆኖ ከዚህ ውስጥ 108,163 ዶላሩ በብር በባንክ መኖሩ ከባንክ ማስራጃ የሚያቀርብ ሲሆን 100 ሺህ ዶላሩ በአይነት መቅረብ የሚችል ሆኖ ንብረቱ በባለስልጣኑ ባለሙያዎች የሚረጋገጥ ይሆናል፣

መጋቢት 30 ቀን 2011 ዓ.ም

መኮንን አበራ

የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር

አባሪ 1

## ከዉጭ አገር ኩባንያዎች ጋር በጋራ ኢንቨስትመንት "Joint Investment" በእቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ዉክልና ስራ ለመስራት የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት በሚፈልጉ አመልካቾች የሚሞላ ቅጽ

የጋራ ኢንቨስትመንት ኩባንያው ስም--------------------------------------------

አድራሻ ፡- ከተማ-------------------ክ/ከተማ-----------------ወረዳ-------------የቤት ቁጥር---------
ስልክ ቁጥር--------------ፋክስ----------------ኢሜይል-------------------

የብቃት ማረጋገጫ የጠየቁበት የስራ ዘርፍ የ(X) ምልክት ያድርጉ

ሀ. የእቃ አስተላላፊነት ☐

ለ. የመርከብ ውክልና ☐

ሐ. ሁለቱንም በጋራ ☐

የስራ አስኪያጁ ስም---------------------------

እኔ ከላይ ስሜ የተጠቀሰው የ------------------------------------------ኩባንያ ስራ አስኪያጅ ከባለስልጣን መ/ቤቱ በ-------------------------የስራ ዘርፍ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንዲሰጠኝ እያመለከትኩ ወደ ስራ ከገባሁ በኋላ፡-

1. ባለስልጣን መ/ቤቱ በሚዘጋጀው የሪፖርት ስርዓት መሰረት በየዕለቱ የሚጠበቅብኝን ሪፖርት የማቀርብ መሆኑን፤
2. በሀገሪቱ ዘመናዊ የሎጅስቲክስ ስርዓት ለመፍጠር አጋዥ የሆኑ እና በመስፈርቱ የተቀመጡ የሶፍት ዌር፤የቴክኖሎጂ፤የማሽነሪ ዓይነቶችን በሚቀርብልኝ ቅጽ መሰረት ሞልቼ የማቅረብ መሆኑን፤
3. የቢሮም ሆነ የተርሚናል አድራሻ ለውጥ በማደርግበት ጊዜ ለባለስልጣን መ/ቤቱ በጽሁፍ የማቀርብ መሆኑን፤
4. ባለስልጣን መ/ቤቱ በሚያዘጋጀው የኢንስፔክሽን ፕሮግራም ጊዜ አስፈላጊውን መረጃ እና ማስረጃ ለማቅረብ ዝግጁ መሆኔን፤

በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የአመልካቹ ፊርማ --------------------ቀን-------------------

ቅጹ በትክክል መሞላቱን ያረጋገጠው ባለሙያ ስም------------------------------

ፊርማ-------------------ቀን-------------------

===========================================================================